
# ምዕራፍ ስድስት

## ባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣ መንገዶች




**ከምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ

- ከባህላዊና ዘመናዊው ጉዞ ጋር የተያያዙ ምልክቶች እውቀታችሁን ታዳብራላችሁ፣
- ባህላዊና ዘመናዊውን ጉዞ በኢምቋ ታስረዳላችሁ፣
- ከምንባቡ ውስጥ ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን ትለያላችሁ፣
- ከቁልፍ ምልክቶች ድህረ ቅጽያ አመልካቾችን ትለያላችሁ፣
- የኢምቋ ዐረፍተ ነገር ትሰራላችሁ፣
- የምልክቶችንክፍሎች ትተነትናላችሁ፣
- ስርዓት ጠብቃችሁ ትወያያላችሁ፣
- በኢምቋ ናሙና ሰዋሰው ውስጥ ያሉትን ቅጽሎች ታስረዳላችሁ።


## ቁልፍ ምልክቶች




ባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣ




ረሃብ




መርከብ




ወንበዴ





ዓመት





ጥቂት


ባቡር



አውሮፕላን



መንደር


ዘበኛ



አህያ


መኪና



እግር



በቅሎ


ሃገር


ድካም


ፈረስ



ምቶት


በሽታ


ካርታ/የሃገር

# ክፍለ ትምህርት አንድ

## አይታዊ ንባብ



1. ከላይ የተቀመጡትን ስዕሎች በጥንቃቄ ተመልክታችሁ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ አስረዱ::
2. በስዕሎች መሰረት የመጓጓዥ መንገድ አይነቶች ምንድን ናቸው?

## ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መምህራችሁ በኢምቋ ያቀረቡላችኃል:: መምህራችሁን በጥንቃቄ ተከታትላችሁ ለጥያቄዎች በኢምቋ መልስ ስጡ::

1. ባህላዊ መጓጓዣ መንገዶች ጥቅም ላይ መዋል የጀመሩት መቼ ነው?
2. በባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣ መንገዶች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## አይታዊ ንባብ

ተማሪዎች፤ መምህራችሁ ባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣ መንገዶች የሚለውን ምንባብ ሲያቀርቡላችሁ ሐሳቡን ለመረዳት ከመሞከር ጎን ለጎን፣ የኢምቋ አጠቃቀማቸውን በጥንቃቄ ተመልከቱ::

### ባህላዊና ዘመናዊመጓጓዣ መንገዶች

ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት የነበሩ ሰዎች ከአንዱ ሃገር ወደ ሌላው ሃገር መዘዋወርን እምብዛም የሚያውቁ አልነበረም:: በዚህ ጊዜ አብዛኞቹ ሰዎችም ሙሉ የህይወታቸውን ዘመን የሚያሳልፉት በጥቂት መንደሮች አካባቢ ብቻ ስለነበር ከሁለት ወይም ከሦስት ማይል አልፈው ሄደው አያውቁም ነበር:: እነዚህ ሰዎች ይጓዙ የነበረውም ሲበዛ በእግራቸው፤ አልያም በአህያ፣ በበቅሎና በፈረስ እየታገዙ ነበር:: በእግራቸው ሲጓዙ ከፍተኛ ድካም ይሰማቸዋል:: በአህያ፣ በቅሎና በፈረስ ሲጓዙ ደግሞ ምቾት አይሰማቸውም:: ከዚህም ሌላ በመንገዳቸው ላይ በሽታ፣ ረሃብና የውኃ ጥም ያጋጥማቸዋል:: ይባስ ብሎም የመንገድ ላይ አውሬውና ቀማኛ ወንበዴው አደገኛ ነበር::

በዛሬው ጊዜ ወደ አንድ ሩቅ ሃገር ለመሄድ ቢፈለግ የከፋ ችግር ሊጋጥሞ አይችልም:: ስለሚሄድበትም ቦታ መጽሐፍ አንብቦ አገሩም ወዴት እንደሆነ ካርታ አይቶ ለመረዳት ይቻላል::ከዚያም በቀር ስለሃገሩ የሚጠየቀውን ሁሉ ሊመልስ የሚችል በዚያ ሀገር የነበረ የሚታወቅ ሰው ያጋጥም ይሆናል:: በመሆኑም ያለ አንዳች ችግርና ስጋት በመርከብ ወይም በባቡር አለዚያም በአውሮፕላን ፈጥኖ ለመድረስ ይቻላል:: ወደ አንድ ሃገር ለመድረስ ባቡር፣ መርከብና አውሮፕላን ባይኖር እንኳ በማንኛውም ተሽከርካሪ መኪና ለመጓዝ ይቻላል:: በዚህ አይነት ሁኔታ አንድ መንገደኛ መጠለያና ምግብ እንዲሁም ለወዳጆቹ መልዕክት የሚያደርስለት መልዕክተኛ እንኳን በየቦታው እንደልብ ለማግኘት ይችላል:: መንገደኞችም ከቀማኛ የሚጠብቃቸው ዘበኛ፣ ቢታመሙ የሚያስተምማቸው ሃኪም ያገኛሉ:: እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ቋንቋቸውን የሚያውቅ ሰው በየቦታው ስለሚያጋጥማቸው ለመግባባት አይቸገሩም:: ስሆነም በባቡር ወይም በመርከብ ሆኖ በአንድ ቀን ብዙ ማይሎችን ለመጓዝ ይቻላል:: በአውሮፕላን ደግሞ በግማሽ ቀን አንድ ሃገር ለመድረስ የሚቻልበት ሁኔታ አለ::

በአጠቃላይ ሲታይ ካለፉት አራትና አምስት መቶ ዓመታት ጀምሮ የጉዞ ነገር ቀላል ሆኗል:: ለባህር ላይ ጉዞ የሚያገለግሉ ታላላቅ መርከቦች ተሰርተዋል፡፤ የተለያዩ አይነት ቀላልና ከባድ ባቡሮችም አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው:: ለመጓጓዣ የሚያገለግሉ አውሮፕላኖችም በእያንዳንዱ ሃገር እንደልብ ይገኛሉ::

*ምንጭ:- ከበደ ደስታ፣ ነጭ ጥለት በጥቁር ላይ፣ 1950 ዓ/ም (ተሻሽሎ የቀረበ)*

## መልመጃ አንድ:-

### አይቶ መረዳት

የሚከተሉት ጥያቄዎች በዋናነት በምንባቡ ውስጥ የተማራችኋቸውን ምልክቶች ለመለማመድና ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ምልክቶችና ዐረፍተ ነገሮች አጠቃቀም ግንዛቤያችሁን ለማስፋት ታስበው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በኢምቋ መልሱ::

1. ከምንባቡ ውስጥ የወደዳችሁትን አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ መምህሩ ባቀረቡበት መንገድ በክፍል ውስጥ በኢምቋ አንብቡ::
2. የምንባቡ ዋና ዋና ነጥቦች ጥቀሱ::
3. የምንባቡን መልዕክት በአጭሩ በራሳችሁ አቀራረብ በክፍል ውስጥ አስረዱ::

## መልመጃ ሁለት:-

### የማስታወስ ችሎታ

የሚከተሉትን ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ በኢምቋ መልሱ::

1. በምንባቡ መሰረት ከአምስት መቶ ዓመት በፊት የነበሩ ሰዎች ከቦታ ቦታ ይጓዙ የነበረው በ ………………….፣ ……………………….፣ …………………….ና …………….. ነበር::
2. ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት የነበሩ ሰዎች በእግራቸው ሲጓዙ ………. ይሰማቸዋል::
3. ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት የነበሩ ሰዎች በአህያ፣ በቅሎና ፈረስ ሲጓዙ …….. አይሰማቸውም::
4. በዛሬው ጊዜ በ ………………………፣ ……………………፣……………………… እና …………….. ከአንዱ ቦታ ወደ አንዱ ቦታ ፈጥኖ ለመድረስ ይቻላል::
5. በባቡር ወይም በመርከብ ሆኖ በአንድ ቀን ………. ማይሎችን ለመጓዝ ይቻላል::
6. የጉዞ ነገር ቀላል የሆነው ከ ……………. ጀምሮ ነው::

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## አይታዊ ንባብ

### መልመጃ አንድ፡-

**በቡድን መስራት**

መምህራችሁ በቡድን ይከፋፍሏችኋል፡፡ በቡድን ከተከፋፈላችሁ በኋላ ከተማራችሁት ውጭ የሆኑ ነገር ግን እናንተ የምታውቋቸው ጥንታዊና ዘመናዊ መጓጓዣዎችንበመጥቀስ ተወያዩ፡፡ ከዚያም የውይይታችሁን ውጤት በቡድናችሁ ተወካይ በኩል ለክፍል ጓደኞቻችሁ በኢምቋ አቅርቡ፡፡

### መልመጃ ሁለት፡-

**ዐረፍተ ነገሮች ምስረታ**

የሚከተሉት ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው፡፡ በቃላቱ የተወከሉትን ምልክቶች በመጠቀም የራሳችሁን የኢምቋ ዐረፍተነገር ስሩ፡፡

| | |
|---|---|
| 1. ወንበዴ | 7 መርከብ |
| 2. ጥቂት | 8. መኪና |
| 3. ማይል | 9. ዘበኛ |
| 4. በቅሎ | 10. አውሬ |
| 5. ምኞት | 11. በሽታ |
| 6. ረሃብ | 12. መንደር |

## መልመጃ ሦስት፡-

### ድህረ ቅጽያ አመልካቾች

የሚከተሉት ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው:: በቃላቱ ከተወከሉት መካከል ድህረ ቅጽያ አመልካቾችን በመለየት በክፍል ውስጥ ዓሣዩ::

ምሳሌ፡- ፍሬ

መልስ፡- ፍሬያማ

1. ስኬት
2. ዝናብ
3. ብርድ
4. ሞቃት
5. ውጤት
6. በረሃ

## ክፍለ ትምህርት አራት

### የምልክት ትንታኔ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተማራችኋቸውን ዋና ዋና ምልክቶች ትንተና በክፍል ውስጥ ዓሣዩ::

ምሳሌ፡- ባቡር

1. የእጅ ቅርጽ፡- ከሌባ ጣት፣ ቀለበት ጣትና ትንሽ ጣት በስተቀር የተዘረጉ ጣቶች
2. የእጅ ቅርጽ የሚያርፍበት ቦታ፡- እጅ ላይ
3. የመዳፍ አቅጣጫ፡- ወደ ታች
4. የእጅ እንቅስቃሴ፡- ከግራ ወደ ቀኝና ከቀኝ ወደ ግራ
5. በእጅ የማይገለጹ ክፍሎ፡- ነፃ

# ክፍለ ትምህርት አምስት

## የኢምቋ ሰዋሰው ቅጽል አመልካቾች

ከዚህ በታች የቀረቡትን የኢምቋ ሰዋሰው ናሙናዎችን በጥንቃቄ አጥንታችሁ ከናሙናዎቹ ቀጥሎ የተሰጠውን መልመጃ ስሩ።

1. አማርኛ፡- ቀላል ባቡር ተሰርቷል።

   ኢምቋ፡- ባቡር ቀላል መሰራት።

2. አማርኛ፡- ረጅሙ ሰውዬ መጣ።

   ኢምቋ፡- ሰው ረጅም መምጣት።

3. አማርኛ፡- ቀይ እስክርቢቶ ሰጠኝ።

   ኢምቋ፡- እስክበርቢቶ ቀይ መስጠት።

4. አማርኛ፡- ትልቁ ወንድሜ ተመርቋል።

   ኢምቋ፡- ወንድም ትልቅ መመረቅ።

5. አማርኛ፡- ታታሪ ሰው እወዳለሁ።

   ኢምቋ፡- ሰው ታታሪ መውደድ።


## የቅጽል አመልካቾችን መለየት

ቅጽል ማለት ስምን የሚገልጽ (የስም ገላጭ) ማለት ነው።

በቡድን በመሆን ከላይ በቀረበው የኢምቋ ናሙና ዐረፍተ ነገር ቅጽል አመልካቾችን ለመምህራችሁ ዓሣዩ።

# ምዕራፍ ሰባት

## ውጤታማ የአጠናን ዘዴ




ከምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች


ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፣

- ከውጤታማ የአጠናን ዘዴ ጋር የተያያዙ ምልክቶች ዕውቀታችሁን ታዳብራላችሁ፣
- ውጤታማ የአጠናን ዘዴን በኢምቋ ታስረዳላችሁ፣
- ከምንባቡ ውስጥ ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን ትለያላችሁ፣
- ከቁልፍ ምልክቶች ቅድመ ቅጽያ አመልካቾችን ትለያላችሁ፣
- የኢምቋ ዐረፍተ ነገር ትሰራለችሁ፣
- የምልክቶችን ክፍሎች ትተነትናላችሁ፣
- ስርዓት ጠብቃችሁ ትወያያላችሁ፣
- በኢምቋ ናሙና ሰዋሰው ውስጥ ያሉትን ተውሳከ ግሶች ታስረዳላችሁ፣


## ቁልፍ ምልክቶች



ውጤታማ የአጠናን ዘዴ




መጥላት



ውድቀት




ስኬታማ



ፍቅር





ማጣቀሻ መጽሐፍ




ስልት



ፍላጎት



ወኔ



ቅደምተከተል



ሚስጥር


ግልጽ



ልምድ


ፍሬ ሃሳብ



ዕውቀት




ማስታወሻ




ከልብ መከታተል




የትኩረት አቅጣጫ




ክፍል



ማስተዋል



መጥፎ አመለካከት



መልካም ግንኙነት

# ክፍለ ትምህርት አንድ

## እይታዊ ንባብ



1- ከላይ የተቀመጠውን ስዕል በጥንቃቄ ተመልክታችሁ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ አስረዱ፡፡

2- በስዕሉ መሰረት የትምህርት ጥናት እንዴት ነው?

## ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መምህራችሁ በኢምቋ ያቀረቡላችኃል፡፡ መምህራችሁን በጥንቃቄ ተከታትላችሁ ለጥያቄዎች በኢምቋ መልስ ስጡ፡፡

1. ውጤታማ ጥናት ምን ምን ዘዴዎችን ያካትታል?
2. ለውጤታማ አጠናን ትልቅ አስተዋፅኦ ያለው ነገር ምንድነው?

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ምንባብ

ተማሪዎች፤ መምህራችሁ ውጤታማ የአጠናን ዘዴ የሚለውን ምንባብ ሲያቀርቡላችሁ ሐሳቡን ለመረዳት ከመሞከር ጎን ለጎን፣ የኢምቋ አጠቃቀማቸውን በጥንቃቄ ተመልከቱ::

### ውጤታማ የአጠናን ዘዴ

በትምህርት ህይወታችን ስኬታማ መሆን ከፈለግን በመጀመሪያ ለምንማረው ትምህርት ፍቅርና ፍላጎት እንዲኖረን ማድረግ አለብን:: ለመምህራን ያለን አመለካከትም አዎንታዊ መሆን ይገባል:: እነዚህን ሁለት ቁልፍ ነገሮች በትክክል ከተገበርን በትምህርታችን ውጤታማ የመሆን ሚስጥርን የመጀመሪያ ምዕራፍ አወቅን ማለት ነው:: ምክንያቱም በትምህርት ላይ ፍላጎት ካሳደርንና መምህራንን የምንወድ ከሆነ ትምህርቱን ከልብ ለመከታተልና ያልገባንን ጠይቀን ለመረዳት ወኔ ይኖረናል::

ሌላው መሰረታዊ ነገር ክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት በሚገባበማስታወሻይዞ ከልብ መከታተል ነው:: ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ካልሆነ በስተቀር ከክፍል ፈጽሞ መቅረት የለብንም:: በተደጋጋሚ ከክፍል የምንቀር ከሆነ የሚሰጠው ትምህርት ተከታታይነትና ተያያዥነት ያለው ስለሚሆን ቀጣዩን ርዕስ ለመረዳትና አብሮ ለመሄድ ያስቸግረናል::

እንደዚሁም ይኸው በተደጋጋሚ ከትምህርት ገበታ የመቅረት ጉዳይ በመምህራን ዘንድ ከታወቀ መጥፎ አመለካከት በራሳችን ላይ እንዲፈጠር እናደርጋለን:: ይህም ደግሞ ከመምህራን ጋር እንዲኖረን የምንፈልገውን መልካም ግንኙነት ያሻክርብናል:: እንዲህ ከሆነ ደግሞ ትምህርቱን እየጠላነው እንመጣና መጨረሻ ላይ ግድ የለሽ መሆን እንጀምራለን:: ይህም የውድቀታችን የመጀመሪያ ምዕራፍ ይሆናል::

ቀጣዩ ስራችን የተለያዩ ማጣቀሻ መጽሐፍት መፈለግና ማንበብ ይኖርብናል:: መምህራን ከሚሰጡን ትምህርት ጋር እያዋሃድን የምናዘጋጀው ሰፋ ያለ ግን ደግሞ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ፣ ግልጽና ያልተንዛዛ፣ ዋና ዋና ፍሬ ሃሳቡን ብቻ የያዘ፣ የራሳችን ማስታወሻ ሊኖረን ይገባል::

ማስታወሻ ማዘጋጀት ባይሆንልን ደግሞ፣ ማስታወሻ በጥንቃቄ የመያዝና ያነበቡትን ነገር ነጥብ በነጥብ የማስቀመጥ ችሎታ ካላቸው ተማሪዎች ልምድ መቅሰም አለብን፤ እንዲረዱንም መጠየቅ ይኖርብናል:: አንዳንድ ተማሪዎች በዚህ የተካኑ ናቸው:: ማስታወሻ ሲይዙ አጥንቱን ከስጋው ለይተው፣ ግሳንግሱንና የማያስፈልገውን አበጥረው፣ እጥር-ምጥን ያለ፣ መተው የሌለበትን ፍሬ ነገር ብቻ የያዘ፣ እጅግ ምርጥ ማስታወሻ ያዘጋጃሉ:: ከነዚህ ተማሪዎች ልምድ መቅሰም ብልህነት ነው::

በመጨረሻም የመምህሩን የማስተማር ስልት፣ የትኩረት አቅጣጫውን፣ የፈተና አወጣጥ ዝንባሌውን የመገመት ብቃት ልናዳብር ይገባል:: የፈተና አወጣጥ ዝንባሌውን በማጥናት፣

የት ላይ የበለጠ ትኩረት መስጠት እንደሚፈልግ መገንዘብ ያስፈልጋል። ራሳችንን ለዕውቀትና ለፈተና ስናዘጋጅ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ታሳቢ ማድረግ አለብን። ይህን ከግምት ውስጥ አስገብተን የምንጓዝ ከሆነ ስኬት በእጃችን ነች። ጊዜያችን በከንቱ አይባክንም። በአጭር ጊዜ ውስጥ በበቂ ሁኔታ አጥንተን ብዙ ሳንደክም ውጤታማ እንሆናለን። ሁል ጊዜ የህይወታችን መርህ "አስተውሎ የሚራመድ ረጅም መንገድ ይጓዛል።" የሚል ይሁን።

*ምንጭ፡- አስራት አብርሃም፣ ጎበዝ ተማሪ የመሆን ምስጢር፣2008 ዓ/ም (ተሻሽሎ የቀረበ)*

## መልመጃ አንድ፡-

### አይቶ መረዳት

የሚከተሉት ጥያቄዎች በዋናነት በምንባቡ ውስጥ የተማራችኋቸውን ምልክቶች ለመለማመድና ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ምልክቶችና ዐረፍተ ነገሮች አጠቃቀም ግንዛቤያችሁን ለማስፋት ታስበው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በኢምቋ መልሱ።

1. ከምንባቡ ውስጥ የወደዳችሁትን አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ መምህሩ ባቀረቡበት መንገድ በክፍል ውስጥ በኢምቋ አንብቡ።
2. የምንባቡ ዋና ዋና ነጥቦች ጥቀሱ።
3. የምንባቡን መልዕክት በአጭሩ በራሳችሁ አቀራረብ በክፍል ውስጥ አስረዱ።

## መልመጃ ሁለት፡-

### የማስታወስ ችሎታ

የሚከተሉትን ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ በኢምቋ መልሱ።

1. በትምህርት ህይወታችን ስኬታማ መሆን ከፈለግን በመጀመሪያ ………….. ማድረግ አለብን።
2. በተደጋጋሚ ከክፍል የምንቀር ከሆነ …………….. ያስቸግረናል።
3. በማስታወሻ ደብተራችን የምንይዛቸው ጉዳዮች …………….. ናቸው።
4. ማስታወሻ ማዘጋጀት ካልቻልን …………. አለብን።

5. ራሳችንን ለፈተና ስናዘጋጅ ................. አለብን።

## ክፍለ ትምህርት ሦስት

### የቡድን ስራ

#### መልመጃ አንድ፡-

በቡድን መስራት

መምራችሁ በቡድን ይከፋፍሏችኋል። በቡድን ከተከፋፈላችሁ በኋላ እያንዳንዳችሁ ትምህርታችሁን እንዴት እንደምታጠኑ ተወያዩ። ከዚያም የውይይታችሁን ውጤት በቡድናችሁ ተወካይ በኩል ለክፍል ጓደኞቻችሁ በኢምቋ አቅርቡ።

#### መልመጃ ሁለት፡-

ዐረፍተ ነገር ምስረታ

የሚከተሉት ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው። በቃላቱ የተወከሉትን ምልክቶች በመጠቀም የራሳችሁን የኢምቋ ዐረፍተነገር ስሩ።

1. ስኬት
2. ፍላጎት
3. ሚስጥር
4. ክፍል
5. መጥናት
6. ውድቀት
7. ግልጽ
8. ፍሬ ሃሳብ
9. ልምድ
10. ፍቅር
11. ዕውቀት
12. ማስተዋል

## መልመጃ ሦስት፡-

### ቅድመ ቅጽያ መልካቾች

የሚከተሉት ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው። በቃላቱ ከተወከሉት መካከል ቅድመ ቅጽያ አመልካቾችን በመለየት በክፍል ውስጥ ዓሣዩ።

ምሳሌ፡-

የጥናት

መልስ "የ" የሚለው ቅድመ ቅጽያ ነው

1. የቤት
2. ለቤት
3. ወደ ቤት
4. ከቤት
5. እስከ ቤት
6. በቤት

## ክፍለ ትምህርት አራት

### የምልክቶች ትንታኔ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተማራችኋቸውን ዋና ዋና ምልክቶች ትንተና በክፍል ውስጥ ዓሣዩ።

ምሳሌ፡-

ፍላጎት

1. የእጅ ቅርጽ፡- "ሽ" ወይም "ግጥም 5 ቁጥር"
2. የእጅ ቅርጽ የሚያርፍበት ቦታ፡- በደረት ትይዩ አየር ላይ
3. የመዳፍ አቅጣጫ፡- ትይዩ
4. የእጅ እንቅስቃሴ፡- ወደፊትና ወደ ኋላ

5. በእጅ የማይገለጹ ክፍሎች፦ የጓን የፊት ገጽታ

## ክፍለ ትምህርት አምስት

### የኢምቋ ሰዋስው ተውሳከ ግስ አመልካቾች

ከዚህ በታች የቀረቡትን የኢምቋ ሰዋስው ናሙናዎችን በጥንቃቄ አጥንታችሁ ከናሙናዎቹ ቀጥሎ የተሰጠውን መልመጃ ስሩ፡፡

1. አማርኛ፡- ሃይሌ በፍጥነት ይሮጣል፡፡

   ኢምቋ፡- ሃይሌ መሮጥ ፍጥነት፡፡

2. አማርኛ፡- ባቡሩ አሁን ይመጣል፡፡

   ኢምቋ፡- ባቡር መምጣት አሁን፡፡

3. አማርኛ፡- ሕፃኑ ቶሎ ይተኛል፡፡

   ኢምቋ፡- ሕፃን መተኛት ቶሎ፡፡

4. አማርኛ፡- ውሻ በጣም ይጮሃል፡፡

   ኢምቋ፡- ውሻው መጮህ በጣም

5. አማርኛ፡- ኤሊ በዝግታ ትሄዳለች፡፡

   ኢምቋ፡- ኤሊ መሄድ ዝግታ፡፡


## የተውሳከ ግስ አመልካቾችን መለየት

ተውሳከ ግስ ማለት ከግስ በፊት ወይም በኋላ እየገባ የግሱን ሁኔታ የሚያሳይ የግስ ገላጭ ማለት ነው፡፡

በቡድን በመሆን ከላይ በቀረበው የኢምቋ ናሙና ዐረፍተ ነገር ተውሳከ ግስ አመልካቾን ለመምህራችሁ ዓሣዩ፡፡

# ምዕራፍ ስምንት

## የከተሞች ታሪካዊ ጠቀሜታ



ከምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፣

» ከከተማ ጋር የተያያዙ ምልክቶች እውቀታችሁን ታዳብራላችሁ።

» የከተማን አስፈላጊነት በኢምቋ ታስረዳላችሁ።

» ከምንባቡ ውስጥ ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን ታስረዳላችሁ።

» የጥምር ምልክቶችን ከጥንድ ምልክቶች ትመሰርታላችሁ።


» የኢምቋ ዐረፍተ ነገር ትሰራላችሁ።

» የምልክቶችን ክፍሎች ትተነትናላችሁ።


» ስርዓት ጠብቃችሁ ትወያያላችሁ።

» በኢምቋ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ያሉትን መስተዋድድ አመልካቾች ትለያላችሁ።

## ቁልፍ ምልክቶች




ከተማ




ሳንቲም




ተፈጥሮ




ገበያ




ሥልጣኔ



የውሃ መስመር



ጥንታዊ




ግንብ




ቁፋሮ




ሮሐ




አክሱም




የመንግሥት አሰራር




ገጠር




የንግድና ኢኮኖሚ ሁኔታ




ሐረር



ጎንደር



ንግድ




አዲስ አበባ



አምልኮ



አደባባይ




## ክፍለ ትምህርት አንድ

### እይታዊ ንባብ



1. ከላይ የተቀመጡትን ስዕሎች በጥንቃቄ ተመልክታችሁ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ አስረዱ::
2. በስዕሉ መሰረት በከተማና በገጠር መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

## ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መምህራችሁ በኢምቋ ያቀረቡላችኃል:: መምህራችሁን በጥንቃቄ ተከታትላችሁ ለጥያቄዎች በኢምቋ መልስ ስጡ::

1. ከተማ ለታሪክ የሚጠቅመው በምን በምን መልኩ ነው?
2. በኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠቀሜታ ያላቸው ከተሞች እነማን ናቸው?

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ምንባብ

ተማሪዎች፤ መምህራችሁ የከተሞች ታሪካዊ ጠቀሜታ የሚለውን ምንባብ ሲያቀርቡላችሁ ሐሳቡን ለመረዳት ከመሞከር ጎን ለጎን፣ የኢምቋ አጠቃቀማቸውን በጥንቃቄ ተመልከቱ።

### የከተሞች ታሪካዊ ጠቀሜታ

በተፈጥሮ ካልተገኙና የሰው ልጅ ከፈጠራቸው ከማይንቀሳቀሱ የሥልጣኔ ውጤቶች አንዱ ከተማ ነው። ከተማ የአንድ ሕዝብ ሥልጣኔ የሚታይበትና የሚቀላጠፍበት ማዕከል ነው። በዚህም የተነሳ የሰው ልጆችን ታሪካዊ ሂደት በመመዝገብና የደረሱበትንም በማሳየት ረገድ የከተማን ያህል የተሻለ ቦታ የለም።

የጥንታዊ ሰዎችን ሥልጣኔ ታሪክ የሚያጠኑ ባለሙያዎች የጉዞውን ሂደት የሚገልጡ መረጃዎችን የሚያገኙት በቁፋሮ ከሚገኙ ጥንታውያን ከተሞች ነው። በእነዚህ ጥንታውያን ከተሞች የሰው አኗኗር፣ ታሪክ፣ የመንግሥት አሰራር፣ የንግድና የኢኮኖሚ ሁኔታ፣ ወግና ስርዓት፣ እምነትና ባህል በተሰናሰለና ስርዓት በጠበቀ መንገድ ይገኝባቸዋል።

በአብዛኛው የገጠሩ ማህበረሰብ ባልተሰባሰበ፣ አንድ ወገን በሆነ፣ ግልጽ የአኗኗር መርሕ፣ አስተዳደራዊ መዋቅር አምብዛም ባልተዘረጋበት መንገድ የሚኖር ነው። የከተማ ማህበረሰብ ግን በተወሰነ ቦታ፣ ከተለያየ ማኅበረሰብ ተወጣጥቶ፣ በአንድ ውሱን ሕግ እየተዳደረ፣ ለክዋኔዎች ቦታ ወስኖ (ለንግድ፣ ለአምልኮ፣ ለመንግሥት አስተዳደር፣ ለመኖሪያ ወዘተ) የሚኖር በመሆኑ የሥልጣኔ መገለጫዎች በከተሞች የሚገኙትን ያህል በገጠር አናገኛቸውም። ሐውልቶች፣ አደባባዮች፣ አብያተ መንግሥት፣ ሳንቲሞች፣ የኪነ ጥበብ ሕንፃዎች፣ የተደራጁ ገበያዎች፣ የውኃ መስመሮች፣ የከተማ መከለያ ግንቦች፣ የእምነት ማዕከሎች በከፍተኛ የሥልጣኔ ደረጃ ተሰርተው የምናገናቸው በከተሞች አካባቢ ነው።

በሀገራችንም የታሪክና ቅርስ ማዕከል የሆኑትን አክሱምን፣ ሮሐን፣ ሐረርን፣ ጎንደርን፣ አንኮበርን፣ አዲስ አበባን፣ ሌሎችንም ብንመለከት የመንግሥት፣ የኢኮኖሚና፣ የእምነት መናኸሪያ ከተሞች ነበሩ፤ ናቸውም። በእነዚህ ቦታዎች የምናገኛቸውን የተሰናሰሉና የተመጋገቡ የሥልጣኔ መገለጫዎችን ያህል በሌሎች ቦታዎች አናገኝም። በሌሎች ቦታዎች የምናገኛቸው በተናጠል የተቀመጡ የሥልጣኔ መገለጫዎችን ነው።

*ምንጭ፡- ዳንኤል ክብረት፣ የሰርቆ አደሮች ስብሰባ፣ 2009 ዓ/ም፣ (ተሻሽሎ የቀረበ)*

## መልመጃ አንድ፡-

### ስዕሳዊ ዕይታን መረዳት

የሚከተሉት ጥያቄዎች በዋናነት በምንባቡ ውስጥ የተማራችኋቸውን ምልክቶች ለመለማመድና ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ምልክቶችና ዐረፍተ ነገሮች አጠቃቀም ግንዛቤያችሁን ለማስፋት ታስበው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በኢምቁ መልሱ፡፡

1. ከምንባቡ ውስጥ የወደዳችሁትን አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ መምህሩ ባቀረቡበት መንገድ በክፍል ውስጥ በኢምቁ አንብቡ፡፡
2. የምንባቡ ዋና ዋና ነጥቦች ጥቀሱ፡፡
3. የምንባቡን መልዕክት በአጭሩ በራሳችሁ አቀራረብ በክፍል ውስጥ አስረዱ፡፡

## መልመጃ ሁለት፡-

### የማስታወስ ችሎታ

የሚከተሉትን ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ በኢምቁ መልሱ፡፡

1. በምንባቡ መሰረት የሰው ልጅ ከፈጠራቸውና ከማይንቀሳቀሱ የሥልጣኔ ውጤቶች አንዱ ………… ነው፡፡
2. በጥንታዊ ከተሞች ውስጥ ………….፣………………..፣………………..፣……….. እና ……….. ይገኙባቸዋል፡፡
3. በሃገራችን ኢትዮጵያ የታሪክና የቅርፅ ማዕከል የሆኑ ከተሞች …………………፣…………….፣………………..፣…………..፣…………፣……………… ወዘተ ናቸው፡፡
4. በከተሞች የሚገኙት መረጃዎች በአብዛኛው  የገጠሩ ማኅበረሰብ ሊገኙ የማይችሉት የገጠሩ ማኅበረሰብ ………፣……………፣…………….፣……… ወዘተ ስለሆኑ ነው፡፡

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## የቡድን ስራ

### መልመጃ አንድ፡-

**በቡድን መስራት**

መምህራችሁ በቡድን ይከፋፍሏችኋል፡፡ በቡድን ከተከፋፈላችሁ በኃላ መስማት ለተሳናቸው ወገኖች ሕይወት መሻሻል ይበልጥ አመቺ የሆነው ከተማ ነው ወይስ ገጠር በሚለው ዙሪያ በቡድን ተወያዩ፡፡ ከዚያም የውይይታችሁን ውጤት በቡድናችሁ ተወካይ በኩል ለክፍል ጓደኞችሁ በኢምቋ አቅርቡ፡፡

### መልመጃ ሁለት፡-

**ዐረፍተ ነገር ምስረታ**

የሚከተሉት ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው፡፡ በቃላቱ የተወከሉትን ምልክቶች በመጠቀም የራሳችሁን የኢምቋ ዐረፍተነገር ስሩ፡፡

1. ተፈጥሮ
2. ጥንታዊ
3. ንግድ
4. አምልኮ
5. ሐውልት
6. አደባባይ
7. ሳንቲም
8. ግንብ
9. አክሱም
10. ሐረር
11. ህንፃ
12. አዲስ አበባ

## መልመጃ ሦስት፡-

### የጥምር ምልክቶች ምስረታ

የሚከተሉት ጥንድ ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው። ጥንድ ቃላቱ ሲጣመሩ የሚሰጡትን ትርጉምበክፍል ውስጥ ዓሣዩ።

ምሳሌ፡- ቤት + መንግሥት

መልስ፡- ቤተመንግሥት

1. ሕግ + መንግሥት
2. ቤተ + መጽሐፍ
3. ቤተ + ክርስቲያን
4. ስም + ጥሩ
5. ክፍል + ሃገር

## ክፍለ ትምህርት አራት

### የምልክቶች ትንታኔ

ምሳሌ፡- አምልኮ

1. የእጅ ቅርጽ፡- የተጨበጡ እጆች
2. የእጅ ቅርጽየሚያርፍበት ቦታ፡- በደረት ትክክል አየር ላይ
3. የመዳፍ አቅጣጫ፡- ትይዩ ነው ወይም ቀኙ ወደ ግራ ግራው ወደ ቀኝ
4. የእጅ እንቅስቃሴ፡- ምንም እንቅስቃሴ የለውም
5. በእጅ የማይገለጹ ክፍሎች፡- የተጨፈነ አይን

# ክፍለ ትምህርት አምስት

## በኢምቋ ዐረፍተ ነገር መስተዋድዶችን መለየት

ከዚህ በታች የቀረቡትን የኢምቋ ሰዋሰው ናሙናዎችን በጥንቃቄ አጥንታችሁ ከናሙናዎቹ ቀጥሎ የተሰጠውን መልመጃ ስሩ፡፡

1. አማርኛ፡- መሐመድና ሙሃባ ትናንት ተጋቡ፡፡

   ኢምቋ፡- መሐመድና ሙሃባ መጋባት ትናንት፡፡

2. አማርኛ፡- ለእኔ ወይም ለአንተ ሎተሪው ይደርሳል፡፡

   ኢምቋ፡- እኔ ወይም አንተ መድረስ ሎተሪ፡፡

3. አማርኛ፡- ከጫልቱ ጋር እማራለሁ፡፡

   ኢምቋ፡- ጫልቱ ጋር መማር፡፡

4. አማርኛ፡- ምትኩ ከምሳ በፊት መጣ፡፡

   ኢምቋ፡- ምትኩ በፊት መጣ ምሳ፡፡

5. አማርኛ፡- ት/ቤት ከክረምት በኋላ ይከፈታል፡፡

   ኢምቋ፡- ት/ቤት በኋላ መክፈት ክረምት፡፡


## የኢምቋ ዐረፍተ ነገር መስተዋድዶችን መለየት

መስተዋድድ ማለት ቃልና ቃልን የሚያገናኝ (የሚያዋድድ) ማለት ነው፡፡

በቡድን በመሆን ከላይ ከቀረቡት የኢምቋ ናሙና ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ መስተዋድድ አመልካቾችን ለይታችሁ ለመምህራችሁ ዓሣዩ፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## የንብ አካል ክፍሎችና ተግባራቸው




ከምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፣

» ከንብ አካላትና ጥቅም ጋር የተያያዙ ምልክቶች ዕውቀታችሁን ታዳብራላችሁ፣
» የንብ አካላትና ጥቅምን በኢምቋ ታስረዳላችሁ፣
» ከምንባቡ ውስጥ ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን ታስረዳላችሁ፣
» ምልክቶችን እንደአገባባቸው ትለያላችሁ፣
» በኢምቋ ዐረፍተ ነገር ትሰራላችሁ፣
» ስርዓት ጠብቃችሁ ትወያያላችሁ፣
» የኢምቋ ዐረፍተ ነገር አይነቶችን ትለያላችሁ፣


## ቁልፍ ምልክቶች




የንብ አካላትና ጥቅም




ቀንድ




ግንባር




መደነቅ




መተንፈሻ አካል




ቀጭን



መናደፍ



ማር




አበባ




ማሽተት




መዳሰስ



ውድ




መስማት




ፀጉር




ሞቃት




አጥጋቢ




በቂ




ክንፍ



እግር



ቀፎ

| | |
|---|---|
|  አትክልት | |

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### እይታዊ ንባብ







1. ከላይ የተቀመጡትን ስዕሎች በጥንቃቄ ተመልክታችሁ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ አስረዱ::
2. በስዕሉ መሠረት ንቦች፣አበቦችና ቀፎዎች ያላቸው ግንኙነት ምንድን ነው?

## ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መምህራችሁ በኢምቋ ያቀርቡላችኃል:: መምህራችሁን በጥንቃቄ ተከታትላችሁ ለጥያቄዎች በኢምቋ መልስ ስጡ::

1. የአንድ ንብ የአካል ክፍሎች ምን ምን ናቸው?

2. ንብ ማር የምታመርተው በየትኛው የአካል ክፍሏ ነው?

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ምንባብ

ተማሪዎች፤ መምህራችሁ የንብ አካል ክፍሎችና ተግባራቸው የሚለውን ምንባብ ሲያቀርቡላችሁ ሐሳቡን ለመረዳት ከመሞከር ጎን ለጎን፣ የኢምቂ አጠቃቀማቸውን በጥንቃቄ ተመልከቱ፡፡

### የንብ አካል ክፍሎችና ተግባራቸው

የንብ አካላት አሰራር ድንቅ ነው፡፡ አካላቷ በሦስት ክፍል ይከፈላል፡፡ አንደኛው ክፍል በግንባሯ በስተቀኝና በስተግራ በኩል ያሉት ቀንድ መሰል ሁለት ቀጫጭን ነገሮች ናቸው፡፡ እነዚህ አካላት ንቧ የምታሸትባቸው፣ የምትዳስስባቸውና የምተሰማባቸው ናቸው፡፡

ሁለተኛው የአካላቷ ክፍል ስድስት ጠጉራም እግሮችና ሁለት ወፈር ያሉ ክንፎች ናቸው፡፡ እነዚህ አካላት ንቧ በአበባ ውስጥ ያለውን ፈሳሽ ነገር መጥጣ የምታመጣባቸው ናቸው፡፡

ሦስተኛውየአካላቷ ክፍል አንጓ ያላቸው መተንፈሻዎች ሲሆኑ፣ በእነዚህ አካላቷ የምትናደፍባቸውና የተበላሸውን ፈሳሽ ነገር የምታስወጣበት ነው፡፡

ንብ ለሰው ጠቃሚ የሆነች ትንሽ ፍጥረት ናት፡፡ በብዙ ጥረት ወጥታ-ወርዳ ብላ የሚያስፈልጋትን ቅስመ አበባ (የአበባ ቅስም) ሰብስባ ጥሩ ማር ሰርታ ያለውድ በግድ ለሰው ታስረክባለች፡፡ ንብ ይህንን ጥቅም የምትሰጠውም ሴቴና ወንዴ የሆኑትን የአበባ ዱቄቶች በእግሯ እየወሰደች እንዲያፈሩ በማገናኘት ነው፡፡

አንድ ሰራተኛ የሚሰራበትን መሳሪያና የሚሰራውን ስራ አሰሪው ካላዘጋጀለት፣ ሰራተኛው ለባለቤቱ አጥጋቢ ነገርን ለመስራት አይችልም፡፡ እንደዚሁም ሁሉ ንብ የሚያስፈልጋትን ነገርካላደረገላት በቂ ማርን አትሰራም፡፡ ለንብ የሚያስፈልገው ነገርም ብዙ ልዩ ልዩ አበቦች በሚገኙበት ቦታ ለመኖሪያዋም ሞቃት የሆነውን ቀፎ በአትክልቱ ውስጥ እያስገቡ መስቀል ወይም ማስቀመጥ ነው፡፡ ስለዚህ አናቢ የንብ ኑሮን የሚያሻሽልበትን ዘዴ እየፈለገና እያጠና ሊሰራ ይገባል፡፡

*ምንጭ፡- ተክለማርያም ፋንታዬ፣ኖህተ ጥበብ ዘሥነ ጽሁፍ፣ 1950 ዓ/ም፣ (ተሻሽሎ የቀረበ)*

## መልመጃ አንድ:-

### አይቶ መረዳት

የሚከተሉት ጥያቄዎች በዋናነት በምንባቡ ውስጥ የተማራችኋቸውን ምልክቶች ለመለማመድና ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ምልክቶችና ዐረፍተ ነገሮች አጠቃቀም ግንዛቤያችሁን ለማስፋት ታስበው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በኢምቋ መልሱ::

1. ከምንባቡ ውስጥ የወደዳችሁትን አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ መምህሩ ባቀረቡበት መንገድ በክፍል ውስጥ በኢምቋ አንብቡ::
2. የምንባቡ ዋና ዋና ነጥቦች ጥቀሱ::
3. የምንባቡን መልዕክት በአጭሩ በራሳችሁ አቀራረብ በክፍል ውስጥ አስረዱ::

## መልመጃ ሁለት:-

### የማስታወስ ችሎታ

የሚከተሉትን ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ በኢምቋ መልሱ::

1. በምንባቡ መሰረት የንብ አካላት አንደኛው ክፍል የሚያገለግለው ..........፣ ......... እና .................. ነው::
2. የንብ ሁለተኛው አካል የሚጠቅመው ለ .................... ነው::
3. የንብ ሦስተኛው አካል የሚጠቅመው ለ ......... እና ............ ነው::
4. ንብ ማር የምትሰጠው ............. ማገናኘት ነው::
5. ለንብ የሚያስፈልገው ነገር .................. ነው::

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## የቡድን ስራ

### መልመጃ አንድ፡-

በቡድን መስራት

መምህራችሁ በቡድን ይከፋፍሏችኋል፡፡ በቡድን ከተከፋፈላችሁ በኋላ የንብን አስፈላጊነትና የቢንቢን አላስፈላጊነት ተወያዩ፡፡ ከዚያም የውይይታችሁን ውጤት በቡድናችሁ ተወካይ በኩል ለክፍል ጓደኞቻችሁ በኢምቋ አቅርቡ፡፡

### መልመጃ ሁለት፡-

ዐረፍተ ነገር ምስረታ

የሚከተሉት ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው፡፡ በቃላቱ የተወከሉትን ምልክቶች በመጠቀም የራሳችሁን የኢምቋ ዐረፍተነገር ስሩ፡፡

| | |
|---|---|
| 1. መደነቅ | 7 ማር |
| 2. ቀንድ | 8 በቂ |
| 3. ማሽተት | 9 ቀፎ |
| 4. ክንፍ | 10 አትክልት |
| 5. አበባ | 11 ክፍል |
| 6. ፈሳሽ | 12 መናደፍ |

## መልመጃ ሦስት:-

### የምልክቶች አገባብ

የሚከተሉት የተሰመረባቸው ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው:: ከቃላቱ ስር ያሉት የቃላቱን አገባብ የሚያሳዩ ናቸው:: የተሰመረባቸው ቃላት በአገባባቸው ሲታዩ የሚያሳዩትን የምልክቶች ልዩነት በክፍል ውስጥ ዓሣዩ::

1. መውሰድ
   - ለዕቃ
   - ለመድሃኒት
2. መሄድ
   - በእግር
   - በመኪና
   - በአውሮፕላን
3. መፈለግ
   - ለጠፋ ነገር
   - ለፍላጎት
   - ለምኞት
4. መፈተን
   - ለፈተና
   - ለምርምር
   - ለችግር
5. ማማር
   - ለመልክ
   - ለዕቃ

## ክፍለ ትምህርት አራት

### የምልክቶች ትንታኔ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተማራችኋቸውን ዋና ዋና ምልክቶች ትንተና በክፍል ውስጥ ዓሣዩ::

ምሳሌ:- ቀጭን

1. የእጅ ቅርጽ:- ከትንሿ ጣት በስተቀር ሌሎችን ማጣፍ
2. የእጅ ቅርጽ የሚያርፍበት ቦታ:- ከደረት ፊት ለፊት
3. የመዳፍ አቅጣጫ:- ወደፊት
4. የእጅ እንቅስቃሴ:- ከላይ ወደ ታች
5. በእጅ የማይገለጹ ክፍሎች:- ሁለቱን ጉንጮች ወደ ውስጥ መምጠጥ

# ክፍለ ትምህርት አምስት

## የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮችን አይነት መለየት

ከዚህ በታች የቀረቡትን የኢምቋ ሰዋሰው ናሙናዎችን በጥንቃቄ አጥንታችሁ ከናሙናዎቹ ቀጥሎ የተሰጠውን መልመጃ ስሩ፡፡

1. አማርኛ፡- ደራርቱ ቆንጆ ልጅ ናት፡፡

   ኢምቋ፡- ደራርቱ ልጅ ቆንጆ፡፡

2. አማርኛ፡- መመሪያውን መከተል አለብህ፡፡

   ኢምቋ፡- መመሪያ አለብህ መከተል፡፡

3. አማርኛ፡- ከልመና መስራት ይሻላል፡፡

   ኢምቋ፡- ልመና መሻል መስራት፡፡

4. አማርኛ፡- የበረሃ ትርጉሙ ሞቃት ነው፡፡

   ኢምቋ፡- በርሃ ትርጉም ሞቃት፡፡

5. አማርኛ፡- እሰይ! ፈተናውን አለፍኩ፡፡

   ኢምቋ፡- ማለፍ ፈተና፡፡


## የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮችን መለየት

ዐረፍተ ነገሮች ገላጭ፣ ትዕዛዛዊ፣ አወዳዳሪ፣ በያኝ እና ቃለ አጋኖ ተብለው ሊለዩ ይችላሉ፡፡

በቡድን በመሆን ከላይ ከቀረቡት የኢምቋ ናሙና ዐረፍተ ነገሮች መካከል የትኛው ገላጭ፣ ትዕዛዛዊ፣ አወዳዳሪ፣ በያኝ ወይም ቃለ አጋኖ እንደሆነ ከምክንያቱ ጋር ለመምህራችሁ ዓሣዩ፡፡

# ምዕራፍ አስር

## የመረጃ አስተማማኝነት የሚረጋገጥባቸው መንገዶች




### ከምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዘህ ትምህርት በኋላ፣


- ከመረጃ ጋር የተያያዙ ምልክቶች ዕውቀታችሁን ታዳብራላችሁ፣
- አስተማማኝና ትክክለኛ የመረጃ ምንጭን በኢምቋ ታስረዳላችሁ፣
- ከምንባቡ ውስጥ ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን ታስረዳላችሁ፣
- ጽንሰ ሃሳብ የያዙ ቃላትን በኢምቋ የጣት ፊደላት ታሳያላችሁ፣
- የኢምቋ ዐረፍተ ነገር ትሰራላችሁ፣
- የምልክቶችን ክፍሎች ትተነትናላችሁ፣
- ስርዓት ጠብቃችሁ ትወያያላችሁ፣
- የኢምቋ ጥያቄያዊ ዐረፍተ ነገሮችን ትለያላችሁ፣

## ቁልፍ ምልክቶች



መረጃ



አስተማማኝ


ወቅታዊ


ማስረዳት



ቴክኖሎጂ


ማወዳደር



ትክክለኛ



መቀስቀስ



ፖሊሲ



ማሳተም



ማሰራጨት



መጽሐፍ


የመንግሥት አካላት


ማመዛዘን



የህክምና ተቋማት


መመርመር


ጋዜጣ




ተዓማኒ




መጽሔት



ኢንተርኔት



ከሙያ አንፃር



ደንበኛ ተኮር

# ክፍለ ትምህርት አንድ

## እይታዊ ንባብ




1. ከላይ የተቀመጡትን ስዕሎች በጥንቃቄ ተመልክታችሁ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ አስረዱ።
2. በስዕሉ መሰረት የመረጃ ማግኛ ዘዴዎች አከፋፈል እንዴት ነው

## ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መምህራችሁ በኢምቋ ያቀረቡላችኃል። መምህራችሁን በጥንቃቄ ተከታትላችሁ ለጥያቄዎች በኢምቋ መልስ ስጡ።

1. አንድ መረጃ አስተማማኝ መሆኑን በምን ይረጋገጣል?
2. አንድ መረጃ ግልፅና አስተማማኝ እንዲሆን የሚፃፍበት ቋንቋ ምን አይነት ቢሆን ይመረጣል?

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ምንባብ

ተማሪዎች፤ መምህራችሁ የመረጃ አስተማማኝነት የሚረጋገጥባቸው መንገዶች የሚለውን ምንባብ ሲያቀርቡላችሁ ሐሳቡን ለመረዳት ከመሞከር ጎን ለጎን፣ የኢ-ምቁ አጠቃቀማቸውን በጥንቃቄ ተመልከቱ።

### የመረጃ አስተማማኝነት የሚረጋገጥባቸው መንገዶች

አስተማማኝና ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ይቻል ዘንድ የተለያዩ መንገዶች ቀርበዋል። ከእነዚህ መንገዶች መካከል የመጀመሪያው የመረጃው አይነትና መረጃውን ያሳተመውና ያሰራጨው አካል ነው። የመንግሥት አካላት፣ የህክምና ተቋማት፣ የመገናኛ ብዙሃን ድርጅቶች፣ ዩኒቨርስቲዎችና ታዋቂ ግለሰቦች ተአማኝነት ያላቸውን መረጃዎች አትመው ያሰራጫሉ ተብሎ ይገመታል። እነዚህ አካላት መረጃዎችን በተለያዩ መንገዶች ማለትም በመጽሐፍት፣ በጋዜጦች፣ በመጽሔቶች፣ በድረ- ገፆችና በመገናኛ ብዙሃን ሊያሰራጩ ይችላሉ።

ሁለተኛ መንገድ የመረጃው ወቅታዊነት ነው። አንዳንድ መረጃዎች ወቅታዊ ሲሆኑ፣ ሌሎች ደግሞ ጊዜ ያለፈባቸው ሊሆኑ ይችላሉ። የመረጃ ማሰራጫ ቴክኖሎጂዎች፣ ፖሊሲዎችና አገልግሎት መስጫ ተቋማት በየጊዜው ሊለዋወጥ ስለሚችሉ ወቅታዊ መረጃዎችን ማግኘት ያስፈልጋል። ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘት ደግሞ መጽሐፍቱ፣ ጋዜጦችና መጽሔቶች የታተመበትን ጊዜያት ወቅታዊነት ማየት ያስፈልጋል። ከድረ-ገጽ የሚገኙ መረጃዎችም ቢሆኑ የቅርብ ጊዜ ህትመት ውጤቶችን የያዙ መሆናቸው መረጋገጥ አለበት።

ሦስተኛው መንገድ ደግሞ የመረጃውን ዓላማ ማወቅ ነው። አንድ መረጃ ዓላማው ነገሮችን ለመግለጽ፣ አንድን ክስተት ለማስረዳት፣ ነገሮችን ለማወዳደር፣ ቅስቀሳ ለማድረግ፣ መመሪያ ለመስጠት፣ ብያኔ ለማሳየት ወይም ለመወያየት ሊሆን ይችላል። መረጃው ምንም ይሁን ምን ዓላማ ሊኖረው ይገባል ማለት ነው። አንዳንዴም በተመሳሳይ ዓላማ የተለያዩ መረጃዎች ሊኖሩ ይችላሉ። በዚህን ጊዜ ሁሉንም አይነት መረጃዎች ሰብስቦ መገንዘብ፣ መጠየቅ፣ ማመዛዘን፣ መመርመርና ማመሳከር ያስፈልጋል። ከዚያም የላሻለውንና ተዓማኒነት ያለውን መረጃ ብቻ መርጦ መጠቀም ይቻላል። ከዚህ አንፃር በኢንተርኔት የሚገኙ መረጃዎችን በጥንቃቄ መርምሮ ጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋል።

የመጨረሻው መንገድ መረጃው የተፃፈበት የቋንቋ አይነት ነው። በመሰረቱ አንድ መረጃ በተለያዩ የአጻጻፍ ዘይቤዎች ሊፃፍ ይችላል። አንዳንዱ መረጃ ከሙያ አንፃር ብቻ ስለሚፃፍ፣ የቋንቋ አጠቃቀሙ ሙያ ተኮር ነው። ሌላው ደንበኛ ተኮር የሚባለው ነው። ደንበኛ ተኮር ቋንቋ አጠቃቀም ሲባል፣ መረጃውን ባለሙያው ብቻ ሳይሆን ደንበኛውም በሚገባ እንዲረዳው የሚያስችል መንገድ ማለት ነው። አንድ መረጃ ሙሉ በሙሉ በሙያ ተኮር ቋንቋ ከቀረበ መረጃው የተፃፈለት ደንበኛ መልዕክቱን ላይረዳው ይችላል። ስለዚህ መረጃው የተፃፈው ለደንበኞች ከሆነ ደንበኛ ተኮር የሆኑ ቃላትና አገላለፆችን መጠቀም ያስፈልጋል።

*ምንጭ፡- www// አስተማማኝ መረጃ፣ 2010 ዓ/ም፣ (ከእንግሊዝኛ ድረ ገፅ ላይ ተተርጉሞ የቀረበ)*

## መልመጃ አንድ፡-

### አይቶ መረዳት

የሚከተሉት ጥያቄዎች በዋናነት በምንባቡ ውስጥ የተማራችኋቸውን ምልክቶች ለመለማመድና ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ምልክቶችና ዐረፍተ ነገሮች አጠቃቀም ግንዛቤያችሁን ለማስፋት ታስበው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በኢምቁ መልሱ።

1. ከምንባቡ ውስጥ የወደዳችሁትን አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ መምህሩ ባቀረቡበት መንገድ በክፍል ውስጥ በኢምቁ አንብቡ።
2. የምንባቡ ዋና ዋና ነጥቦች ጥቀሱ።
3. የምንባቡን መልዕክት በአጭሩ በራሳችሁ አቀራረብ በክፍል ውስጥ አስረዱ።

## መልመጃ ሁለት፡-

### የማስታወስ ችሎታ

የሚከተሉትን ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ በኢምቁ መልሱ።

1. በምንባቡ መሰረት ተአማኒነት ያላቸውን መረጃዎች ያሰራጫሉ ተብለው የሚገመቱት .......፣ ..............፣.......................፣............. እና .......... ናቸው።
2. አስተማማኝና ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት የሚያስችለው ሁለተኛው መንገድ ..................... ነው።
3. የአንድ መረጃ ዓላማ .......................፣.....................፣.................. ፣.......................፣ ................ ወይም ............ ሊሆን ይችላል።
4. አንድን መረጃ መመርመርና ማመሳከር የሚያስፈልገው ለ ................... ነው።
5. አንድን መረጃ ባለሙያው ብቻ ሳይሆን ደንበኛውም ሊረዳው የሚችለው በ ............ ቋንቋ ሲፃፍ ነው፡

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## የቡድን ስራ

### መልመጃ አንድ:-

**በቡድን መስራት**

መምህራችሁ በቡድን ይከፋፍሏችኋል። በቡድን ከተከፋፈላችሁ በኃላ ለመስማት የተሳናቸው ሰዎች አስፈላጊ በሚባሉት የመረጃ ምንጮች ላይ ተወያዩ። ከዚያም የውይይታችሁን ውጤት በቡድናችሁ ተወካይ በኩል ለክፍል ጓደኞቻችሁ በኢምቋ አቅርቡ።

### መልመጃ ሁለት:-

**ዐረፍተ ነገር ምስረታ**

የሚከተሉት ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው። በቃላቱ የተወከሉትን ምልክቶች በመጠቀም የራሳችሁን የኢምቋ ዐረፍተነገር ስሩ።

| | |
|---|---|
| 1. አስተማማኝ | 7. ወቅታዊ |
| 2. ማስረጨት | 8 ኢንተርኔት |
| 3. መጽሐፍ | 9 ቴክኖሎጂ |
| 4. ድረ- ገጽ | 10 መቀስቀስ |
| 5. ጋዜጣ | 11 ፖሊሲ |
| 6. መመርመር | 12 ብያኔ |

## መልመጃ ሦስት፡-

### የጽንሰ ሃሳብ የጣት ፊደላት

የሚከተሉት ጽንሰ ሃሳቦች የጣት ፊደላትን ወክለው የተቀመጡ ናቸው:: የጽንሰ ሃሳቦቹን የኢምቋ የጣት ፊደላት በክፍል ውስጥ ዓሣዩ::

ምሳሌ፡- ተውኔት

መልስ፡- ተ_ው_ ኔ_ት

| | |
|---|---|
| 1. ቢሮክራሲ | 7. አስትሮኖሚ |
| 2. ዳያሌክቲክስ | 8 ቶርቸር |
| 3. ዳይኖሰር | 9 ግሎባላይዜሽን |
| 4. ኢያንደርታል | 10 ኢምፔሪያሊዝም |
| 5. ትውፊት | 11 አይዲያሊዝም |
| 6. ልህቀት | 12. ሜሪኩሪ |

## ክፍለ ትምህርት አራት

### የምልክቶች ትንታኔ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተማራችኋቸውን ዋና ዋና ምልክቶች ትንተና በክፍል ውስጥ ዓሣዩ::

ምሳሌ፡- ማሰራጨት

1. የእጅ ቅርጽ፡- ከወደ ጫፍ የተጨበጡ እጆች
2. የእጅ ቅርጽ የሚያርፍበት ቦታ፡- ከደረት ፊት ለፊት
3. የመዳፍ አቅጣጫ፡- ወደ ታች
4. የእጅ እንቅስቃሴ፡- ወደ ግራና ወደ ቀኝ
5. በእጅ የማይገለጹ ክፍሎች፡- ፊት ለፊት

# ክፍለ ትምህርት አምስት

## የኢምቋ ጠያቂ ዐረፍተ ነገሮች ምልክቶችን መለየት

ከዚህ በታች የቀረቡትን የኢምቋ ሰዋሰው ናሙናዎችን በጥንቃቄ አጥንታችሁ ከናሙናዎቹ ቀጥሎ የተሰጠውን መልመጃ ስሩ::

1. አማርኛ፡- ያንተ ስም ማን ነው?

   ኢምቋ፡- አንተ ስም ማ::

2. አማርኛ፡- አንቺ የት ነው የምትኖሪው?

   ኢምቋ፡- አንቺ መኖር የት::

3. አማርኛ፡- ሽማግሌው ዕድሜው ስንት ነው?

   ኢምቋ፡- ሽማግሌ ዕድሜ ስንት::

4. አማርኛ፡- ሳሙና እንዴት ይሰራል?

   ኢምቋ፡- ሳሙና መስራት እንዴት::

5. አማርኛ፡- የኢትዮጵያ አዲስ አመት መቼ ይጀመራል?

   ኢምቋ፡- አዲስ አመት ኢትዮጵያ መጀመር መቼ::

## የኢምቋ ጠያቂ ዐረፍተ ነገሮችን መለየት

ጠያቂ ዐረፍተ ነገር ማለት ነው? መቼ? ማን? እንዴት? የሚሉ ጥያቄዎች የቀረቡበት ማለት ነው::

በቡድን በመሆን ከላይ ከቀረቡት የኢምቋ ናሙና ዐረፍተ ነገሮች ጠያቂ ምልክቶች ለይታችሁ ለመምህራችሁ ዓሣዩ::

# የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

# 9ኛ ክፍል

የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር